# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**የሕፃናት አገልግሎት ፕሮግራም**

በሚቀጥለው ቅዳሜ (June 15 @ 3 p.m.) እሕፃናት ያዘጋጁት የጸሎትና የቃል ትምህርት ጊዜ ተዘጋጅቷል። እህቶች ሁሉ ለዚህ ፕሮግራም በቤተ ክርስቲያን ተገናኝታችሁ እንድትካፈሉ የአገልግሎቱ መሪዎች ያሳስባሉ። ወንድሞች ደግሞ ልጆችን በመጠበቅ እንድትተባበሩ እናሳስባለን።

**በችካጎና አካባቢው አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት የተዘጋጀ የፒክኒክ ፕሮግራም**

በ June22, 2019 በችካጎና አካባቢው አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት የተዘጋጀ የፒክኒክ ፕሮግራም ስለሚኖረን ሁላችንም ለመገኘት ጊዜአችንን እንድናመቻች እናሳስባለን። ይህ ፕሮግራም ታላቅ የሕብረት ጊዜ እንደሚሆንልን እናስባለን።

**በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት**

- ቀን፡ 7/4 - 7/6/2019
- ስልክ፡ (920) 294-3323 Booking ID number= 14589 or Yemsrach
- በዚህ ፕሮግራም ፓስተር አሳየኸኝ በርሄ ያገለግለናል።
- እሳካሁን 58 አዋቂዎችና 60 ልጆች ተመዝግበዋል። ሪዘርቭ ያደረግናቸውን ክፍሎችን በMay 3 ስለምንለቅ ያልተመዘገባችሁ ተመዝገቡ።
- በዚህ ፕሮግራም ጨዋታዎችን በማቀድና በማስተባበር ለማገልግል የምትፈልጉ ስማችሁን ለረድኤቱ እንድትሰጡ እንጠይቃለን።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**

773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጻደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10




"መንፈስ ድካማችንን ያግዛል::"
(ሮሜ. 8:26)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.

**June 9, 2019**

**ሰኔ 2፣ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ቃል ............. | ፓስተር ኃይለልዑል እምሩ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።” (ሮሜ 8:11)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ጴጥሮስ መኩሪያ

### <u>የተለየ ሕዝብ</u>

*“እናንተ ግን ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ ፤ ለእርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ።” (1ኛ ጴጥ. 2፡9)*

እግዚአብሔር አባታችን ምን ዓይነት ሹመት እንደሰጠንና እርሱ እንዴት እንደሚያየን ማስተዋል ለትክክለኛ የእምነት አቋም ወሳኝ ነው። በምድር ላይ ካሉት ሰዎች በሙሉ እግዚአብሔር በጸጋው የለየን ሕዝብ ነን። ይህ ደግም እኛ እንደፈለግነው፣ እንደሚሰማንና እንደሚታየን እንድንኖር ሳይሆን በምድር ያለነው በዓላማ እንድንኖር ነው። ንጉስ ዳዊት በዘመኑ የእግዚአብሔርን ሃሳብ እንዳገለገለ እኛም በዘመናችን የእርሱን በጎነት ለማወጅ ተጠርተናል።

አምላካችንና አባታችን በፀጋ በጌታ ኢየሱስ ልጆቹ ካደረገን በኋላ ወደ እውነት የሚመራውን መንፈስ ቅዱስን በውስጣችን አኖረው። እግዚአብሔር በፍጥረት መጀመሪያ የፍጥረቱ በኩራን ከነበሩት ከአዳምና ከሔዋን ጋር የነበረውን አይነት ኅብረት ከእያንዳንዱ በጌታ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት አድርጎ ከወለዳቸው ልጆቹ ጋር እንዲኖረው ይፈልጋል። ለዚሁም ሁልጊዜ በፊቱ እንድነገኝ እጅግ ይሻል። በጸሎት ፊቱን በመሻትና ሕያው ቃሉን በመመገብ ከእርሱ ጋር የጠበቀና የማያቋርጥ ኅብረት ሲኖረን እርሱን በበለጠ ክብር እናየዋለን፤ ኃይልን እንቀበላለን፤ በአእምሮአችንም መታደስ እንለወጣለን። ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን በአእምሮአችን መታደስ ስንለወጥ የእግዚአብሔር ፍቃድ ምን እንደሆነ ፈትነን እናውቃለን ደግሞም የዓለምን አስተሳሰብ በመናቅ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል እናድጋለን። (ሮሜ. 12፡1-2)

በመጽሐፈ በመሳፍንት ምዕራፍ 6 ላይ ስንመለከት ጌዲዮን የሚባለው ሰው እራሱን የሚመለከተው ፈሪ፤ ነገሮች ያልተሳኩለት፤ ሁል ጊዜ ተገዝቶ የሚኖር፤ የበታች የሆነ ሰው አድርጎ ነበር። ከሁሉ የሚገርመውና የሚያሳዝነው የእስራኤል ሕዝብ የአምላካቸውን ቃል ካለመፈለግ የተነሳ በምድያማውያን መገዛታቸውንና መጠቃታቸውን አለማስተዋሉና በበለጠ ደግሞ ከነሙሴና ከእነ ኢያሱ ጋር የነበረው ኤልሻዳዩ አላካቸው ኃይሉ እንዳልቀነሰ ገልበቱ እንዳልላላ፤ ማስተዋሉም ዛሬም የማይመረመር መሆኑን መዘንጋቱ ነው። እግዚአብሔር ግን በዚህ ሰው ውስጥ የተመለከተው ጽኑና ኃያል የሆነ የእስራኤል አዳኝ ነበር። እንዲሁም ሙሴ የታየው የእርሱ ኮልታፋነት ሲሆን እግዚአብሔር ግን የታየው ሕዝቡን ከፈረዖን እጅ ነፃ የሚያወጣ የእርሱን የጊዜው መሳሪያ ነበር። ዳዊት በሌሎች የታየው እንደ አንድ የበጎች እረኛ ሲሆን እግዚአብሔር ግን የታየው አንድ የሕዝቡ የጊዜው ታዳጊ ነበር። እግዚአብሔር በያንዳንዳችን ውስጥም የሚያየው ለእርሱ አላማ ለመኖር የተለዩ፤ የእርሱን በጎነት የሚያውጁ ቅዱሳን ወንድና ሴት ልጆችን ነው።

ቅዱሳን ወንድሞችና እሕቶች፡- እኛስ እራሳችንን እንዴት ነው የምናየው? ምንም ሁኔታ ይሁን፤ የበረታ የጠላት ጦር ይሁን፤ ድል የተነሳው ዲያቢሎስ ይሁን ከእነርሱ ጋር ያለው ኃይል፣ ጥበብና እውቀት ከእኛ ጋር ካለው ከኤልሻዳዩ አምላካችን አይበልጥም። ሁሉም ያሉት በጊዜአቸው ለእኛ ትምህርት ሆነው ሊሸነፉ ነው። በጌታ ኢየሱስ የዳነ ሰው አሸናፊ ነው። እኛ ልንገዛ፣ ልንበዛ፣ ለበረከት፣ የምድር ጨውና ብረሃን ለመሆን ከማይጠፋ ዘር ተወልደናል። ለተፈጠርንበት ዓላማ ለመኖር የሚያስፈልገን ሙሉ ጸጋና ሥልጣን ተሰጥቶናል። በተጨማሪም ጌታን እንደ ግል አዳኝ አድርገን ስንቀበል የጥበብ፣ የማስተዋል፣ የዕውቀት፣ እንቆቅልሽን የመፍታትና የገዥነት መንፈስ ተሰጥቶናል። እግዚአብሄር እውነተኛ ማንነታችንን በመረዳት ይባርከን። እኛም በመረዳትና በውሳኔ ይህንን የተጠራንበትን የድል ሕይወት በሥልጣን እንኑር። አሜን!